# ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ

## Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity

Efdpu@aol.com www.Finote.org


በፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ራዲዮ
በጥቅምት 27 ቀን 2010 ዓም የተላለፈ ሀተታ

## ኢትዮጵያ በየካቲት 1966 ዓም እና በመስከረም 2010 ዓም መካከል ያለፈው ስህተት እንዳይደገም፤ ምን መደረግ አለበት ?

ከአያሌ ዘመናት የግፍ አገዛዝ በኋላ፤ የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመጀመሪያ ጊዜ ገዥዎቹን፤ ያለ ማንም ርዳታ በገዛ እጁ ከሥልጣን ያወረደበት ዘመን 1966 ዓም ነው ። ይኸንን ድል የተቀዳጀው ከአፅናፍ እስከ አፅናፍ ሁሉም ዜጋ ተባብሮ በአንድ ላይ በመቆሙ ነበር ። ይኸ የጋራ ሀገራዊ ድል የተገኘው፤በጎሣ፤ በቋንቋ ፤ በሃይማኖትና በርዕዮት ሳይከፋፈል፤በአንድ ልሳን በመጮኽ፤ በአንድ ልብ በማመንና፤ አንድ ራዕይ በማየት መሆኑ ማንም አይክደውም። በወቅቱ የነበሩት የማኅበራዊና የመንግሥታዊ ሠራተኞች ተቋማት ፤ ህዝባዊና ባኅላዊ ድርጅቶች ሳይቀሩ ፤ ሁሉም ኢትዮጵያዊ- ሀገራዊ አንድነትንና ዕምነትን ያነገቡ ነበሩ ። ከዚኽ ሃቅ በመነሳታቸው ለትግላቸው አንድነት ጽኑ መሠረት እንዲያገኙ አስችሏቸዋል ። በዚያን ጊዜ በነበረው ክስተት፤ የሕዝባዊው ዕመፅ የኃይል ሚዛንና አሰላለፉን ማስታወሱ ለዛሬው ትግል ከሞላ -ጎደል፤ ለግንዛቤ ግዙፍ ርዳታ ያደርጋል።

ሀ / 1ኛ. የኢትዮጵያ ሠርተኞች ማህበራት ኮንፌዴሬሽን

2ኛ. የኢትዮጵያ መምኅራን ማኅበር

3ኛ. የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበር እና የዩኒቨርሲቲ መምኅራን ማኅበር አባላት

4ኛ. የኢትዮጵያ ዐርበርኞች ማኅበር ፤

ለዐብነት ተጠቃሾች ናቸው ።

አደረጃጀታቸውና ዐላማቸው በኢትዮጵያ ሕዝብ እኩልነትና ሀገራዊ አንድነት ላይ የተመሠረተ ነበር።

ለ/ መንግሥታዊ ተቋማት

1ኛ. መለዮ ለባሹ ፡- ዐላማውና ተልዕኮው የሀገር መከላከያ ተግባርን መፈፀም ነበር፤

2ኛ. የሚኒስቴር መ/ቤቶች የበታች ሹማምንትና ሠራተኞች ፤በሀገራዊ አንድነት ላይ ቀናዒ ነበር

3ኛ. በልዩ ልዩ ድርጅቶችና የሙያ ማኅበራት የተሰባሰቡ ኃይሎች የመላውን ዜጋ ምኞት አፀባራቂዎች ነበሩ ።

በ ሀ እና በለ የተጠቀሱት በአንድ ላይ ሲደመሩ፤ ዐላማቸው፤በሀገር አንድነት ላይ ያተኮረ በመሆኑ ፤ **ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ አርቆ ተመልካች ራዕይ** ነበረው ።

ከግማሽ ምዕተ -ዐመት በኋላ ያለቸው ኢትዮጵያ ነባረዊ ሁኔታ ግን የነበረውን ሁሉ የሚፃረር ሆኖ ተገኝቷል። ዘውግና ቋንቋ ተኮር በሆነ ፖለቲካ ተቀይሯል ።ሀገራዊ የነበረው ራዕይ ፤ በክልል ሸለቆ ውስጥ ገብቷል። በዘር አጥር ተከብቧል። በዐለም አቀፍ መነፅር ፤ ከአድማስ ባሻገር መመልከቱ እየቀረ፤ ሁሉም ወደ ማጀቱ ለመግባት እየተሽቀዳደመ ይገኛል ። የዕምነት መሪዎች ሳይቀሩ፤ " ሄዳችሁ፤ወንጌልን/ እምነትን ከአጽናፍ አጽናፍ አስተምሩ " የተባለውን ሃይማኖታዊ መርሕን በመጣስ ፤ " አክሱም ፅዮንን አትንኩብን " የሚል ፊሊፕ ይሰብካሉ።

የዛሬይቱ ኢትዮጵያ፤ ሃይማኖትንና ፖለቲካውን ብቻ ሳይሆን፤ ስፖርትን፤ ሙዚቃን፤ ሥነ ጽሁፍን፤ ልሣነ ጥበብን ሁሉ ሳይቀር፤ የዘር መናኻሪያ፤ የዜጎች መራኮቻ፤ የሀገር መገንጠያ የሚተገበርባት ምድር ሆናለች። ሥነ ኃሳብ ( አይዲዮሎጅ) ሳይቀር፤ ለሰብዐዊ ፍጡር ጥቅምና ደኅነነት ማስተማሪያ መሆኑ እየቀረ፤ የዘረኝነትን ዕኩይ ተግባራት መስፈፀሚያ እንዲያገለግል ሆኖ ተቀምሯል። በዛሬይቱ ኢትዮጵያ፤ የሚከተለቱ ቋንቋ ነክ ተቋማት ተዘጋጅተው፤ ለሀገሪቱ መፈረካከሻ መሳሪያዎች ሆነዋል። የማጥፋት ተልዕኳቸውንም በትጋት በመፈፀም ላይ ይገኛሉ ። እነርሱም፡-

**1ኛ. ሀ.** የመከላከያ ሠራዊት የሚባለው አደረጃጀቱ፤ በአማዘኙ ከአንድ አናሳ ብሄር የተውጣጣ ነው፤ ከጓድ/ መቁርስ ጀምሮ ፤ በልዩ ልዩ ዕርከን ያሉትን ወታደራዊ መዋቅሩንና አሰላለፉን፤ የትዕዛዝ ሰንሰለቱንና ሥምሪቱን፤ ከሥልጠናው እስከ ትጥቁ ድረስ የሚቆጣጠሩት የአንድ ንኡስ ብሄር አባላት ናቸው።

**ለ.** በዘመናዊቷ ኢትዮጵያ የመንግሥት ታሪክ ውስጥ፤ ተወዳዳሪ አይገኝለትም የሚባለለት የስለላ ድርጅት/ ኢንተለጀንስ ቢሮ መሪዎቹና አባላቱ ፤ እንደዚሁ ፤ ከአንድ ብሄር የተወጣጡ ናቸው ። ተልዕኳቸውም ፤ የዘረኞችን ስትራተጂያዊ ግብ ለመስፈፀምና የገዥዎቹን ሥልጣን ዕድሜ ለመጠበቅ ነው። ጠቃዋሚያቸውን ሁሉ ድምጥማጡን ማጥፋት ፤ የመጀመሪያው ተልዕኳቸው ነው።

**2ኛ.** የሠራተኛው ማኅበራትና ሲቪል ድርጅቶች፤ ሃይማኖታዊ ተቋማትና ሰባኪያን ፤ በሀገራዊ ዕሴት ሳይሆን፤ በዘውግ ላይ የተመሠረተ አደረጃጀት ስር ወድቀዋል ። የማነኛውም ሃይማኖት ምዕመናን ፤ ስብሳቢና ጠባቂ የላቸውም። **" መንጋዎች ዕረኛ አላገኙም "**

**3**ኛ. ዝናንና ክብርን፤ ተጎናጽፈው ፤ ለመላዋ ሀገርና ሕዝብ ጥቅም ሲባል ተደራጅተው የለወጥ ሐዋርያት የነበሩት ፤ የኢትዮጵያ መምሕራንና የኢትዮጵያ ተማሪዎች ማኅበራት ፤ ሀገራዊ ሰብዕናቸው ተደምስሦ፤ በየጎሳቸው እንዲደራጁ ተደርገዋል ። ይህ ደግሞ ፤ የመምሕርነትን ሙያ ክብር አዋርዶታል። የትምህርትንም ደረጃና መርኀ አርክሶታል።

**4ኛ.** ጳጳሳቱና ሰባኪያን ሳይቀሩ በየዘራቸውና ጎሳቸው ተፈርጀው ተደልድለዋል። የፖለቲካ መሳርያና አገልጋይ ሆነዋል። " **የቄሳርን ለቄሳር ፤ የመለኮትን ለመለኮት** " የሚለው ሃይማኖታዊ ምርኅ ተረስቷል።

**5ኛ.** የእነኝኽ ሁሉ ድምር ውጤት ዐላማው፤ ያው ዞሮ-ዞሮ፤ ኢትዮጵያ እንደ አንድ ሀገር፤ ሕዝቦቿም እንደ አንድ ሕዝብ መኖር አያስፈልጋቸውም የሚለውን የወያኔን ህልም ዕውን ለማደረግ የታለመ ቅዠት ነው ። ቅዠቱ ግን አይሳካም ። ለጊዜው ብቻ፤ በሕዝቡ ፤የአንድነት ትግል ላይ ሳንካ መፍጠሩ አልቀረም። ለተወሰነ ወቅትም ቢሆን፤ ወያኔ በሥልጡኑ ተንጠልጥሎ ለመወራጨት ይጥቅመዋል ። ሁለቱን ዐበይት ብሄሮችን፤ ዕርስ በዕርስ ለማፋጀት የሚካሄደው ወንጀል፤ ብልሹ ፖለቲካ ያመጣው ፤ የዘር ማጥፋት (Genocide ) መሆኑ ሊሰመርበት ይገባል ። ዐደጋውን ለመከላከል፤ የመላው ኢትዮጵያ ሕዝብ ዓይነተኛና አጣዳፊ ተግባር መሆኑን ለደቂቃም ቢሆን መዘንጋት የለበትም። ብሄራዊ ወንጀል ሲፈፀም ፤ የተቃውሞ ድምፅ ሳያሰሙ በአርምሞ መመልከት፤ የወንጀሉ ተባባሪ እንደሆነ ይቆጠራል። በህግ ፊት ከመጠየቅ አያድንም።

**" ኦሮሞው ሲጨፈጨፍ ፤ የተቃውሞ ድምፅ አላሰማሁ፤ ኦሮሞ አልነበርኩምና፤! ዐማራው ሲጠፋ ፤ አልተቃውኩም፤ ዐማራ አልነበርኩምና ! አኝዋኩ ሲቃጠል አልጮህኹም፤ አኝዋክ አልነበርኩምና! በመጨረሻ፤ በእኔ በትግሪው ላይ መጡ፤ የሚቃወማቸው ሁሉ በጠፋበት ጊዜ ! "** የጥቅሱ መሠረት (Orgion ) የተገኘው በናዜዎች ዘመን ከተነገረው ምኅላ ነው።

በመጠኑም ቢሆን እንኳ ፤ በ1966 ዓም የነበረውንና አሁን በ2010 ዓም ያለውን የሀገራችንን ፖለቲካም ሆነ የኃይል ሚዛን ፤ እንዲሁም ያሰላለፉንም ረድፍ ገላጭ መሆኑን ከተረዳን፤ በወቅቱ ከወደቅንበት የፖለቲካ ድንብርብርና ምስቀልቅል (Quagmire ) ፈንቅሎ መውጣት ሁኔታው አስገዳጅ መሆኑ መረዳት ያስፈልገናል ፡፡ በዘር ላይ የተመሠረተው የፖለቲካ ምኅዳርና አፈፃጸሙ፤ ለሁኔታዎቹ ምስቅልቅልና ውስብስብ መሆን ምክንያት ሆኗል ። ይኽ ችግር አልበቃ ብሎ፤ ሌላ ተጨማሪ ዕዳ ተጨምሮ ፤ ለመፍተሄው ፍለጋ ዕንቅፋት ሆኖብናል ። ይኸውም ፤የሁለት ተፃራሪ አመለካከቶች በአክራሪነት መፋጠጣቸው ነው። የእነኝኽ ሁለት አክራሪዎች መከሰት ፤ ሁለት ፖለቲካዊ ዥዋ-ዥዎች ኅብረተሰቡን የማወድናበት ሚና እንዲጫወቱ አድርጓቸዋል ። እነርሱም በአንድ በኩል፡-

**1ኛው.** ኢትዮጵያን በሃያ አንደኛው ክፍለ ዘመን ፤ እሳቤ ያለማየት ችግር ሲሆን፤

**2ኛው.** ኢትዮጵያ የምትባለውን ሀገር አፍርሶ እንደገና ጠፍጥፎ የመቅረፅ ከንቱ አባዜ የተጠናወታቸው ፅንፈኛ ብሄረተኞች ናቸው።

የሁለቱ አክራሪ ኃይሎች መከሰት፤ መላውን ሕዝብ ግራ ለማጋባት አስችሏቸዋል ። የሁለቱ አክራሪ አመለካከቶች የፖለቲካ ዥዋዥዌ መጫወት፤ በኅብረተሰቡ ዘንድ አሉታዊ አስተጋብኦ ማሳደሩ አልቀረም ። አክራሪነትና ፅንፈኝነት ፤ በመጨረሻ ፤ ተበጣጥሰው እንደሚጠፉ ባይካድም፤በጊዜው ካልተደረሰባቸው ፤ ለሀገርና ሕዝብ በቀላሉ የማይከስም ጠንቅ ትተው እንደሚጠፉ መዘንጋት አይኖርበት ። **"ሳይደርቅ በቅጠል"** ነውና መርዙን እስከነ ጠንቁ ማጥፋት፤ በይደር የሚታለፍ አይደለም። ነገር ከተበላሸ በኋላ ፤ሀዘን ላይ ተቀምጦ ሙሾ መደርደር፤ የሀሚናዎች ሙያ እንጅ፤ የአዋቂ ፖለቲከኞች የተግባር ድርሻ አይደለም ።

በተቃርኖ የተቀመጡ ባላንጣዎች አብረው መኖር አይቻላቸውም። አንዱ ሌላውን ካላጠፋ ፤ዕንቅልፍ አይወስደውም ።

እዚኽ ላይ ፤ አንድ ስመ ጥር ኢትዮጵያዊ ባለቅኔ የተቀኘውን ለመዘከር እንገደዳለን። እንዲኽ ብሎ አንጎራጉሮ ነበር ይባላል !

**" እርሳስና ላጲስ አብረው ይኖራሉ፤ ግብራቸው ተቃርኖ ፤**

**የሚጽፈው ከታች፤ አጥፊው ከላይ ሆኖ ! "**

ታላቁ የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ አጥፊዎቹን ሁሉ፤ **" እያወቀ የሚያጠፋውን ፤ እያስተማርክ ቅጣው"** ይላል እንጅ፤ **" እየሰማ የሞተውን ፤ እያየ ቅበረው ! "** ብሎ አይፈርድበት ። አክራሪ ፅንፈኞች በቀደዱት ቦይ ላለመግባት የሚቻለው፤ ሁሉንም አመለካከት በሚያስተናግድ ፤ በብስለት ላይ የተገነባ የመቻቻል ፖለቲካን ማስተናገድ የተቻለ እንደሆን ነው። ይኽንን ለማድረግ፤ የሀገሪቱን ታሪክና ይዘት፤ የዜጎቿንም ጉራማሌነት በግምት ያስገባ ሥርዓትን ለማስፈን ብቃትና ክኽሎት ሲኖር ብቻ ይሆናል ። ለዚኽ ደግሞ አቸናፊና ተቸናፊ በሚል ቅኝት ሳይገባ፤ **በጋራ ሀገር፤ በጋራ አብሮ መኖር ሊቻል የሚቻልበትን የፖለቲካ ሥር ዓት መቀይስ ሲቻል ብቻ ነው።**

አብሮ ተያይዞ ከመጥፋት ፤ ተባብሮ አንድ ላይ መኖር በብዙ መልኩ ይመረጣል ። የዐደዋን ድል ሁልጊዜ እየተመኙ በተስፋ መኖር ብቻውን መፍተሄ አላመጣልንም። የኢትዮጵያ ሕዝብ ዘወትር፤ በታሪክ ትዝታ ብቻ ዕግር- ተወርች፤ ተደይኖ እንዲኖር መፍቀድ ራሱን የቻለ፤ ብሄራዊ ወንጀል ነው። በታሪክም፤ በትውልድም ዘንድ ያስጠይቃል!

የዛሬዋ የ2010 ዐመተ-ምህረት ኢትዮጵያ፤ በ 1966ቱ ዐመተ ምህርት ከነበረችው ኢትዮጵያ በብዙ መስፈርት የተለች ሀገር መሆኗ ጭራሽ አያከራክርም።

**1ኛ.** የዜጎቿ ቁጥር በ አራት እጅ ጨምሯል ። ዛሬ መቶ ሚሊዮን እንደደረሰ ይነገራል ። የሕዝቡ መልከዐ ምድር (Demography )በመለወጡ አዲስ ትውልድ( Generation ) ተፍጥሯል ።

**2ኛ.** በአለፉት ሃምሳ (50 ) ዐመታት ሦስት ፅንፈኛ አጋዛዞች ተፈራርቀውባታል ። ሁሉም በጥፋት ድርጊታቸው እንጅ የበጎ ተግባር ትውስታን አላተረፉም። ሀገርና ሕዝብ አላመናቸውም ። በዚኽ ምክንያት ፤ የቆዩትን ዘመን ያኽል ቆይተው ሀገር አጥፍተው ጠፍተዋል ። ሀገርና ሕዝብ አውላላ ሜዳ ቀርተዋል ። "ትሻልን እያስወገዱ ትባስን መተካት " የፖለቲካ ባኅላቸን ከሆነ ቆይቷል።

**3ኛ.** የአገዛዝ ለውጦች ቢፈራረቁም፤ የዴሞክራሲ ሥር ዓት መተካት አልተቻለም ። ታግሎ መጣልና ማፍረስ እንጅ ተባብሮ መገንባት አልተሞከረም። አሁን አሁንማ፤ ተባብሮ መግንባት ይቅርና አንድ ላይ ሆኖ አምባገነኖችን ማስውገድ እንኳን አስቸጋሪ ሆኗል ።

**4ኛ.** የኢትዮጵያን ሕዝብ አስተባብሮ በጋራ ዕራይ ላይ እንዲያተኩር የሚያስችለው ብሄራዊና ቋሚ ሠነድ ማዘጋጀት አልተቻለም። በየወቅቱንና በተናጠል የሚጻፉት መግለጫዎች፤ የፖለቲካ ፕሮግራሞች፤ መመሪያዎችና ማኒፌስቶ ዎ ች ፤ ቢጠራቀሙ፤ የኢትዮጵያን ብሄራዊ ሠነድ ያህል ሚዛን አይደፉም ። በተለያዩ አጋጣሚዎች የመንግሥት ሥልጣን የያዙ

አልፎ-ሀጂ አባገነኖች የሚለቀልቁት " ህገመንግሥት" የየግላቸው የመጨቆኛ መሳሪያ ከመሆን አልፎ-ተርፎ ፤ ለኢትዮጵያና ለዜጎቿ ዕርባና አላመጣም ፡፡

ሀገራችን፤ ትውልድና ዘመን ተሻጋሪ ፤ቋሚ፤ ዘለዓለማዊና በዜጎቿ የፀደቅና የተከበረ ብሄራዊ ሠነድ ያስፈልጋታል ፡፡ የእራሷ፤ የግሏ ፤ አንጡራ ኢትዮጵያዊ ማግና-ካርታ (Magna Carta ) ያስፈልጋታል !

**5ኛ.** ቴክኒዮሎጅ ያፈራውን የመገናኛ ብዙሃንን ጥበብና ግልጋሎት እየተጠቀሙ ዜና መለዋወጥ፤ ለመቀራርብን ኃሳቦችን ለማንሸራሸር የሚጫወተው ሚና እንደተጠበቀ ሆኖ ፤እርስ ዕርስ ለመንታረኪያ ከሆነ ፤ ለአንድነትና ኅብረት ለሚደረገው ጥረት ፤ አፍራሽ እንጅ ገንቢ እንዳልሆነ፤ የእስካሁኑ ተመክሯችን ህያው ምስክር ነው፡፡

ወያኔንና አፍራሽ ኃይሎችን ለመቋቋም ፤ የአንደነት ኃይሎች መነታረክ ካልቆመ ፤ ዘረኞችን ከሥልጣናቸው ለማውረድ በሚደረገው ትግል አይጠቅምም፡፡ ጠላቶቻችን ፤ **"እሣትና ገለባ ያድርጋቸው "** እንደሚሉን ማወቅ አለብን፡፡

የኢትዮጵያ ሕዝብ የጠላቶቹን ክፉ ምኞት አምክኖ፤ የቆየውን አንድነቱን አድሶ ፤ተባብሮ ሀገሩን ማዳን የወቅቱ አንገብጋቢ ጥያቄ ነው፡፡ **" ያለፈው ቅራና፤ የሚመጣው መጫኛ "** ነውና ያለፈውን ስኅተት አርሞ ፤ ከጉድለት ተምሮ በአንድ ላይ መነሳት አለበት ! ወያኔ የሚያፈሠውን የሕዝባችንን ንፁህ ደም ለማቆም የጋራ ትግሉን እንዲቀጥል በተማጽንዖ መልክ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን !

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኖራለች !